# ተደራሽ MT BAKER

## የአጭር ጊዜ የእግረኛ መንገድ/የብስክሌት መንገድ ማሻሻያ ስራዎች

FACT SHEET
ሕዳር 2019



Rainier Ave S እና Martin Luther King Jr Way S መሰቀለኛ መንገድ በዋና ዋና መዳረሻዎች መካከል ይገኛል፤ ለምሳሌም የ Mt Baker Link ቀላል ባቡር ጣቢያ፣ የኪንግ ካውንቲ ሜትሮ ትራንዚት ማዕከል፣ Franklin 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ቤቶችና የችርቻሮ ንግድ ቦታዎች ይገኙበታል።

**አጠቃላይ መግለጫ**

የ Mt Baker ጣቢያ አካባቢ ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ የተደረጉ በርካታ ዕቅድ ዝግጅት ሒደቶች ትኩረት የነበረ ሲሆን፣ በዚህም ውስጥ ማህበረሰቡ የበለጸገ፣ ብዝሃነት ያለው፣ ዘላቂና ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ የከተማ ማዕከል እንዲኖረው ያለውን ራዕይ በግልጽ አሰቀምጦ ነበር።

የዚህ ራዕይ አካል የሆነው ደግሞ የተሻሻለ የትራንስፖርት ደህንነትና ትስስር ሲሆን፣ ሰዎች ወደ ትራንዚት ማዕከሉና በ Rainier እና MLK ወደሚገኘው የቀላል ባቡር ጣቢያ ለመድረስ የሚያችላቸው **የአጭር ጊዜ የእግረኛ መንገድ/የብስክሌት መንገድ ማሻሻያ ስራዎች** እያዘጋጀን ነው።

በበፊት አውትሪች መሰረት፣ ሊሆኑ የሚችሉ የአጭር ጊዜ የማሻሻያ ጽንሰ ሃሳቦችን ለይተናል (ከጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት)። በዚህ ዓመት መጨረሻ ላይ፣ በወጪ/ጠቀሜታ እና በማህበረሰቡ ግብዓት መሰረት የትኛውን ወደ ዲዛይን ማሳደግ እንዳለብን እንመርጣለን። የማሻሻያ ስራዎቹን የምንገነባው በ2024 ነው።

**የዳሰሳ ጥናታችንን ይሙሉ!**

በአካባቢው የሚኖሩ፣ የሚሰሩ፣ የሚሸምቱና የሚጓዙ ሰዎችን አስተያየት መስማት እንፈልጋለን። የፕሮጀክት ምርጫ ደረጃዎትን እስከ ታሕሳስ 31 ድረስ በኦንላይን የዳሰሳ ጥናታችን በኩል ያስገቡ!

www.surveymonkey.com/r/AMB_Survey



Mt Baker Hub የአውትሪች ዝግጅት ከ Franklin 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ጋር (ፎቶ፡ Mt Baker Hub)

## ተደራሽ MT BAKER የእግረኛ መንገድ/የብስክሌት መንገድ ማሻሻያ ስራዎች

**ለተጨማሪ መረጃ**

www.seattle.gov/transportation/projects-and-programs/programs/transportation-planning/accessible-mt-baker
AMB@seattle.gov or 206-775-8720

Seattle Department of Transportation
MOVE SEATTLE

እነዚህ ሊሰሩ የታሰቡ የማሻሻያ ስራዎች በግምገማ ላይ ሲሆኑ፣ የሚገነቡትም በ 2024 ነው።




1 የእግረኛ መንገድ ኩርባዎችን ማስፋት |ማለትም፣ "የኩርባ መብራቶችን መግጠም"|

2 የእግረኛ መንገድን ማስፋትና መጠገን

3 የእግረኛ ማቋረጫዎችን ማስፋት

4 የ Mt Baker Blvd ሰሜናዊ ረድፍ ለእግረኛ/ለብስክሌት ብቻ ማድረግ

5 ከ Rainier ወደ MLK በስተሰሜን የሚያልፈው የቀይ መብራት መብት የለውም

6 ለአገረኞች ድልድይ አርቲስቲክ ማስዋቢያዎችን መጨመር

7 አዳዲስ የእግረኛ ማቋረጫዎች መስራት (አሁን ያለውን ምልክት ወደ ሌላ ቦታ ማዛወርን ይጨምራል)!

8 በ Rainier/McClellan እና MLK/McClellan ያሉትን የእግረኛ ማቋረጫዎች ማሻሻል

**ማስታወሻ፡ በዚህ ካርታ ላይ በሚገኙት እያንዳንዱ ዋና ዋና መስቀለኛ መንገድ ላይ "ዋነኛ የእግረኛ መንገድ ክፍተቶች" እየጨመርን ነው። ዋነኛ የእግረኛ መንገድ ክፍተቶች የምልክት ጊዜ ቀያሪዎች ሲሆኑ፣ አሽከርካሪዎች አረንጓዴ መብራት ሳይለቃቸው በፊት እግረኞች መንገዱን እንዲሻገሩ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። እግረኞች ይበልጥ እንዲታዩ በማድረግ ግጭቶችንም ይቀንሳል።**

## ሌላ ተደራሽ የ MT BAKER ስራ

ከአጭር ጊዜ የማሻሻያ ስራዎች በተጨማሪ፣ ወደታላቁ ራዕይ ለማድረስ የሚያግዙን ጥረቶች ላይም እየሰራን ነው፡-

1. ከኪንግ ካውንቲ ሜትሮ እና ሳውንድ ትራንዚት ጋር በመተባበር **የሜትሮ ትራንዚት ማዕከልን ወደ Mt Baker የቀላል ባቡር ጣቢያ አቅራቢያ ማዛወርን** አዋጭነት እናጠናለን። ከበፊት አውትሪች እንደምናውቀው፣ ይህ ለውጥ ተፈካኪ በመሆኑ በቴክኒካዊ ዝርዝሮችና አጋጣሚዎች ጉዳይ ላይ በውስጥ እየሰራን ነው። የዚህ የቦታ ለውጥ የመጀመሪያ ዲዛይን ወጪው የተሸፈነ ሲሆን፣ የመጨረሻው ዲዛይንና ኮንስትራክሽን ወጪ ግን በአሁኑ ጊዜ አልተሸፈነም።
2. ከተለያዩ ኤጀንሲዎች የተውጣጣ ቡድን ጋር በትብብር እየሰራን ሲሆን፡ የቡድኑ ትኩረትም የ **Mt Baker ጣቢያ አካባቢ ዕቅድ ማውጣት** ሆኖ የማህበረሰቡን ራዕይ በተሻለ መልኩ በሚያሳካ መንገድ ኢንቨስትመንቶችን የሚያቀናጁ አዋጭ እና ተጨባጭ እርምጃዎችን መለየት ነው። ይህ ሒደት እየተመራ ያለው በዕቅድ ዝግጅትና በማህበረሰብ ልማት ጽ/ቤት ነው።



Mt Baker የቀላል ባቡር ጣቢያ